# ዝክረ ተኮላ

ጥቅምት 20 ቀን 2015ዓም(30-10-2022)

ለካስ ነበር ማለት እንዲህ ነው! ይህንን የተናገሩት በሴራ ከቤተመንግሥታቸው ተባረው በእንጦጦ ተራራ ላይ በሚገኘው ቤታቸው እንዲቀመጡ የተገደዱት ዝነኛዋ ንግሥት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ነበሩ።እውነትም ጊዜ ይሮጣል፤የነበረው በትዝታ ብቻ ይቀራል።ትዝታው የመልካም ሥራ ወይም የመጥፎ ተግባር ሊሆን ይችላል።ለዚያም ነው ስም ከመቃብር በላይ ይውላል የሚባለው።በበጎነት መነሳትንና መወሳትን የመሰለ ትልቅ ጸጋ የለም።ለዚያ ዕድል የሚበቁት ጥቂቶች ናቸው።ከነዚያ ዕድለኞች መካከል አንዱ ወንድማችንና የትግል ጓዳችን አቶ ተኮላ ወርቁ ነው።ነበር ለማለት ያልደፈርነው አሁንም በማህበራዊ ግንኙነታችንና በትግል ጉዟችን ውስጥ ጥሎልን የሄደው የቆራጥነት፣የአልበገሬነት፣የአገር ወዳድነትና በቃል አክባሪነት የሚከተለው የእውነት መንገድ ትዝታው አብሮን ስላለ ነው።

ላለፉት 50 ዓመታት ፣ገና ከአስራኛው የዕድሜ ገደብና ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ በአገሩ በኢትዮጵያና በውጭ አገር የስደት ኑሮ በትምህርት ቤትና፣በመሥሪያቤት ባሳለፋቸው ዓመታት በአገራችን የሰፈኑትን ጸረ ዴሞክራሲና አምባገነን ሥርዓቶች በመቃወም በተለያዩ ወቅቶች ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ቆመናል ከሚሉት ስብስቦች ጋር በመሆን እስከ እለተ እረፍቱ ድረስ በቃኝ ፣ሰለቸኝ፣ደከመኝ ሳይል ጉልበቱን፣ዕውቀቱን፣ጊዜውንና ገንዘቡን ሳይቆጥብ የሚችለውን ሁሉ አበርክቷል።በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር፣ በኢሕአፓ፣በመድህን፣ በመኢአድ፣በአማራው ሞረሽ ወገኔ፣በአማራው ድምጽ ራዲዮ ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ ያበረከተው ድርሻ ቀላል አልነበረም፤በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ስርጭትም ከመጀመሪያው እለት ጀምሮ እስከ እለተ እረፍቱ ድረስ ያደረገው የብዙ ዓመታት አስተዋጽኦ በስርጭቱ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ ይዟል።ተኮላ ወርቁ ለራሱ ኑሮና ምቾት ትኩረት ሳይሰጥ ሁሉንም ለተሰደደላት ለኢትዮጵያ አገሩ ሲያበረክት መኖሩን እኛም ሆንን ሌሎቹ አብረውት የተሰለፉት የማይክዱት ሃቅ ነው።

ከፖለቲካው ተሳትፎ ባሻገር ስለሰው ልጆች ያለው አመለካከት ዘርና ሃይማኖት፣ጾታ ወይም ዜግነትን የለዩና ለአንድ ወገን ብቻ ያደላ አልነበረም።በምክርም ሆነ በገንዘብ ድጋፍ ለሁሉም ፈጥኖ ደራሽና የጠዩቁትን የሚያደርግ ሰብአዊነትንና ሰውነትን የተላበሰ ደግና እሩህሩህ ነበር።ይህንን በጎ ሥራውን በስዊድን በስደት የሚኖሩ ብዙዎቹ ይመሰክሩለታል። በሙያው መስክ ባገለገለበት መሥሪያ ቤትና የሥራ ጓደኞቹ በችሎታውና በትጉህ ሠራተኝነቱ ምስክርነታቸውን በልዩ ልዩ መልክ በተደጋጋሚ ገልጸውለታል።

ከፖለቲካው ድርሻ በተጨማሪ በኢትዮጵያውያን ማህበረ ነክ እንቅስቃሴም ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።በተለይም በስዊድን ዋና ከተማ በስቶኮልም ውስጥ ብቸኛና የመጀመሪያ የሆነውን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ይዞታ የሆነውን የደብረ ሰላም መድሃኔዓለም ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ያደረገው ጥረትና ለ17 ዓመታት በጸሃፊነት፣ በፋይናንስና አስተዳደር ዙሪያ ደንብ በማስከበር በኩል ያበረከተው ድርሻ ለቤተክርስቲያኒቷ መጠናከርና አሁን ላለችበት ደረጃ እንድትበቃ ግንባር ቀደም መሆኑን የቤተክርስቲያኗ አባቶች፣ዲያቆናትና ምዕመናን አይዘነጉትም።ለዚያም ሲሉ ታሞም ሆነ ከሞተ በኋላ ስሙን እያነሱ ሲዘክሩትና ጸሎተፍትሃት ሲያደርጉለት ቆይተዋል።ለዚህ መንፈሳዊ አገልግሎታቸው ቀሳውስቱንና ምዕመናኑን እንደ ቤተሰቦቹ እኛም የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ክፍለጊዜ አዘጋጅ ለማመስገን እንወዳለን።

አቶ ተኮላ ወርቁ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው የአጭር ጊዜ የኮቪድ በሽታ ምክንያት ህይወቱ ካለፈች ይኸው አንድ ዓመት ሆነው።ይህንኑ የአንድ ዓመት ህልፈቱን በትናንትናው ቀን በኦክቶበር 29 በመቃብር ቦታው አበባ በማስቀመጥ፣ ዛሬ ደግሞ በደብረሰላም መድሃኔዓለም በቤተክርስቲያን ከልጆቹና ከዘመድ አዝማዶቹ ጋር ሆነን ዘክረነዋል።

አቶ ተኮላ ምንም እንኳን በመካከላችን ባይኖርም ስንሰባሰብም ሆነ በግል ለአንድም ቀን ቢሆን ስሙንና ተግባሩን ሳናነሳ ያሳለፍንበት ጊዜ የለም።የተነጋገርነው ቁም ነገርና ያሳለፍነው ጥሩና መጥፎ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ድምጹ ከጆሯችን አልጠፋም።የሃሳብ አገላለጡ፣ሳቁና ቀልዱ ፣ነገራት ከሚጠብቀው ውጭ ሲሆኑበት ወይም አቅጣጫ ሲስቱ የሚያድርበት መከፋት ሳይቀር ከፊታችን ድቅን ይላል።

ለተኮላ ሞት ምክንያቱ የበሽታው ክብደት ብቻ ሳይሆን ለአገሩ ካለው አስተዋጽኦ ጋር በተያያዘው፣የእረፍትና የእንቅልፍ ማጣት፣በዬእለቱ የሚሰማው የወገኖቹ መጨፍጨፍና መፈናቀል፣የአገሩ ሰላምና አንድነት መናጋት ለከፍተኛ ውስጣዊ መዳከም እንደዳረገው፣ ከኮቪድ በሽታ በፊት በምናዬውና በምንሰማው የምንመሰክረው ጉዳይ ነው።

በዬእለቱ ከመደበኛው ሥራው በተጨማሪ ስለአገሩ በመጻፍና ከኢትዮጵያውያን ጋር ረዥም ሰዓት በመወያዬት ስለሚያሳልፍም ለከፍተኛ የወገብ ህመም ተጋልጦ ነበር።

በአካል ተለይቶን ትዝታውን ብቻ ጥሎልን ከሄደ ዛሬ አንድ ዓመት ሞላው።በኦክቶበር 29 ቀን 2021 ዓም ዕለተ ዓርብ በቀኑ 13 ሰዓት ገደማ ላይ በመጨረሻዋ እስትንፋሱ ይህችን ዓለም ተሰናበተ። በኖቬምበር 13 ቀን 2021 ዕለተ ዓርብ፣ከጥቂት ሰዎች ጋር ሆኖ ባቋቋመው በስቶኮልም የመድሃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን የእምነት አባቶች፣ዲያቆናትና፣ ምእመናን፣ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ በተገኙበት የፍትሓተ ጸሎት ስንብት ተከናውኖ ብዙ ሰው በተገኘበት የቀብር ስነስርዓቱ ተፈጸመ።

የሰው ልጅ ሁለት አይነት ሞት ይሞታል።አንዱ ለጊዜያዊ ደስታና ጥቅም ሲል ፣በከፋትና በራስ ወዳድነት ተበክሎ፣ሌላውን በመጉዳትና በማሰቃዬት፣በአገር ክህደት ላይ ተሰልፎ በቀጥታ በንጹሃን ላይ ወንጀል የሚፈጽም ፣ባይፈጽምም አጥፊዎችን ሳይቃወምና ለተበደሉት ሳይጮህ በፍርሃትም ይሁን በመደገፍ ድምጹን ሳያሰማ  የቀረ ጭምር በሥጋ ሳይሆን  በቁሙ የመንፈስ ሞት  የሞተ ነው።ሌላው የሰውነት ክብሩን ሳያጣ ፣ለጊዜያዊ ጥቅም ሳያጎበድድና እጁን ሳይሰጥ፣ለሃቅ ቆሞ፣ለሌሎች ሲታገል ኖሮ  የማይቀረውን ስጋዊ ሞት የሚሞት ነው።የዚህ አይነቱ ሞት ተራ ሞት ሳይሆን ዘለአለማዊ ክብር ጥሎ ማለፍ ማለት ነው።ምክንያቱም  ህያው በሆነ ታሪክ ተከብሮና ተወድሶ ስሙ ከማቃብር በላይ ስለሚኖር እንደ ተራ ሞት አይቆጠርም።በሥጋ  ሞተ እንጂ በመንፈስ ያልሞተ ህያው ነውና!

ተኮላ ወርቁ አሁንም በመካከላችን በመንፈስ አለ፤ወደፊትም አብሮን ይኖራል።የተኮላንና የመሰሎቹን ቅን ኢትዮጵያውያን ነፍስ ይማር እያልን የታገሉለት ዓላማ ከግቡ እንዲደርስ የዘወትር ፍላጎታችንና ጸሎታችን ነው።እኛም በሄዱበት የትግል ጎዳና እዬሄድን የድርሻችንን አበርክተን የዕጣችንን የሞት ጽዋ እስክንቀበል ድረስ ብርታቱን ይስጠን እንላለን።

ወንድማችን ተኮላ ወርቁንና ለአገራቸውና ለወገናቸው ህይወታቸውን ለሰጡትና መከራ ላዩት ጀግና የትግል ጓዶቻችን በየካቲት ወር 2003 ዓም በአገሬ አዲስ በተጻፈው ግጥም ልናወድሳቸው እንወዳለን።

እነዚያ  ታጋዮች

በኂላ ተወልደው ከፊት የቀደሙ፣

ለመስዋዕትነት የተሽቀዳደሙ።

ወይስ ከውሃው ነው ከእህል ከቅጠሉ፣

ከቶ ምን ቢጠጡ?  ከቶ ምን ቢበሉ?

የተጠመቁበት ምንድን ነው ጠበሉ?

ለእኛ ነው እንጂ ለእኔ የማይሉ፣

ከዕድሜያቸው በላይ ባሳብ የበሰሉ፣

እነዚያ ታጋዮች፣ከወዴት ተገኙ? እንደምን በቀሉ?

ለመጥፎ ስርዓት መሳሪያ ሳይሆኑ፣

ጥቅም ሳይገዛቸው ከሕዝብ የወገኑ፣

በጮርቃነት ዕድሜ መስዋእት የሆኑ፣

ወይስ ከነሱ ነው ወይስ ከዘመኑ?

በተማሪው ትግል ተሳትፎ ያደገ፣

በመሳሪያው ትግል ገጠር የመሸገ፣

ቆስሎ የተረፈ በጫካ የሞተ፣

ተሰዶ ተዋርዶ የተንከራተተ።

የዛ ደግ ትውልድ የትግል ቤተሰብ፣

ስራው ምስክር ነው ታሪክ ቢሰበሰብ።

የዛ ጀግና ትውልድ ግራ ዝንባሌ፣

ለዘመኑ ትውልድ ይሆናል ምሳሌ።

በድፍን ኢትዮጵያ ከተማና ገጠር፣

የሰማዕታት ስም ቢጠራ ቢቆጠር፣

አሳልፎ መስጠት ሕይወት ያህል ነገር፣

ምን አይነት ፍቅር ነው ለሕዝብና ላገር?

ጥፋቱ ልማቱ ስራው ቢተነተን ፣

አልተነሳም ነበር አገር ለመበተን።

እነዛ ቆራጦች ብርቱ የነበሩ፣

ወጡ ተሰደዱ ሄዱ በያገሩ።

በደም የተጻፈው ሕያው ታሪካቸው፣

ዘላለም ይኖራል ሲወደስ ስራቸው።

አማራ፣ ጉራጌ፣ኦሮሞና ትግሬ፣

ሶማሌ፣ ከንባታ አፋርና አደሬ፣

አንድ ላይ ያሰማ የትግል ዝማሬ፣

እያለ ኢትዮጵያን ውድ አገሬ፣ክብሬ፣

የጎሳ በሽታ ክልል ያላወረው፣

በአማርኛ ቋንቋ ፊደል የቆጠረው፣

የትም ቦታ ሄዶ ተግባብቶ የኖረው፣

ያ ነው ጀግና ትውልድ ትግል ያፋቀረው።

ለአንድ ዓላማ ቆሞ፣ ተሳስቦ፣ ተስማምቶ፣

ችግሩን  ተካፍሎ፣ ለሌላው ሲል ሞቶ፣

እንዲህ ያለ ትውልድ ዬት ይገኛል ከቶ?

ሃሳባቸው ባይሰምር ትግላቸው ባይቀና፣

የለኮሱት ችቦ የእኩልነት ፋና፣

የቀደዱት መንገድ ያብዮት ጎዳና፣

ደግሞ ያገረሻል ትግል እንደገና፤

ቀን ቆጥሮ ይነሳል ሆኖ አይቀርም መና፣

አዲስ ጀግና ትውልድ ይፈጠራልና!

የሞቱትን ነፍስ ይማርልን!ብርታታቸውንም ያድለን!!